የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ ህዳር ፲ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 6
ADDIS ABABA 19th November, 2018

<u>ማውጫ</u>

ደንብ ቁጥር ፬፻፴፮/፪ሺ፲፩

የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩትን ስልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………………………………….ገፅ ፲ሺ፮፻፳፰

**<u>CONTENT</u>**

Regulation No. 436 /2018

Definition Of Powers, Duties And Organization Of Policy Studies Institute Council of Ministers Regulation…………………………...…page10628

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፴፮/፪ሺ፲፩

## <u>የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩትን ስልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ላይ የተደረገውን ለውጥ ተከትሎ የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት በፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፯/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፴፪(፲፩) መሰረት የተቋቋመ በመሆኑ፣

የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፯/፪ሺ፲፩ መሰረት የኢንስቲትዩቱን ስልጣንና ተግባር በአንድ ላይ በማሰባሰብ የኢንስቲትዩቱን አደረጃጀት መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

ለኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲቲዩት፣ እና ለፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ሁሉ ለፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ተሰጥተዋል በሚል በመቀመጡ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፯/፪ሺ፲፩ ዓ.ም አንቀጽ ፴፬ መሰረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ “የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩትን ስልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፴፮/፪ሺ፲፩ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO. 436/2018

## <u>COUNCIL OF MINISTERS REGULATION FOR DEFINITION OF POWERS, DUTIES AND ORGANIZATION OF POLICY STUDIES INSTITUTE</u>

WHEREAS, Policy Studies Institute is established by Proclamation No. 1097/2018 Article 32(11), following the redefining of the organization, powers and duties of the executive organs of the Federal Democratic Republic Of Ethiopia;

WHEREAS, it is necessary to determine the organization of the Institute by collecting the powers and duties in to one document, as it is provided under the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1097/2018 ;

WHEREAS, it is provided that powers and duties given to the Ethiopian Development Research Institute and Policy Studies and Research Center shall be given to the institute;

NOW, THEREFORE, this Regulation is issued by the council of Ministers pursuant to Article 34 of Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation no.1097/2018.

### 1. <u>Short Title</u>

This Regulation may be cited as the “Definition of Powers, Duties and Organization of Policy Studies Institute “Council of Ministers Regulation No.436 /2018” .

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፪. **<u>ዋና መስሪያ ቤት</u>**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ መ/ቤቶችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

፫. **<u>ዓላማ</u>**

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ የፖሊሲና ስትራቴጂ ሀሳቦችን ማመንጨት እና የፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነዶችን ማዘጋጀት ይሆናል፡፡

፬. **<u>የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በሥራ ላይ ባሉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ ጥናትና ምርምር የማካሄድ፤ ጥልቀትና ወቅታዊነት እንዲኖራቸው የማድረግ፤ በየወቅቱ ያለውን ዕድገትና ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ የፖሊሲና ስትራቴጂ ሀሳቦችን የማመንጨት፤

፪/ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣አዳዲስ የፖሊሲና ስትራቴጂ ሃሳቦችን ማመንጨትና የፖሊሲ ሰነድ ማዘጋጀት፤

፫/ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ያስከተሉትን ውጤት መገምገም፣ በአፈፃፀም ወቅት የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ለመፍታት ጥናትና ምርምር በማካሄድ የመፍትሔ ሀሳብ የማመንጨት፤

፬/ ለሚያካሂደው ጥናትና ምርምር የሚያስፈልጉትን መረጃዎች መሰብሰብና ዳታ ቤዝ ማዘጋጀት፣ በሌሎች አካላት የተሰበሰቡትንም የመጠቀም፤

፭/ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ሥራዎች የሚዳብሩበትን መድረኮች፣ ሴሚናሮች እና ወርክሾፖችን የማዘጋጀት፣ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር አጫጭር ስልጠናዎች የማዘጋጀትና የመስጠት፣ እንደአስፈላጊነቱ የምርምር ውጤቶችን የማሳተምና የማሰራጨት፤

፮/ የፖሊሲና የስትራቴጂ ጉዳዮች ላይ የምክር አገልግሎት የመስጠት፤

፯/ ለዓላማው መሳካት አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ከሚችሉ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ አገር ተቋማት ጋር ግንኙነት የመመስረት፤

፰/ የአገሪቷን ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ለማድረግ ቁርጠኝነት፣ዝግጁነት እውቀትና ፍላጎት ያላቸው ተመራማሪዎችን መፈለግ፣ ማደራጀትና ማብቃት፤

2. **<u>Head office</u>**

The Institute shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

3. **<u>Objectives</u>**

The objective of the Institute shall be to undertake studies and research, initiate policies and strategies and prepare policy and strategy documents.

4. **<u>Powers and Duties of the Institute</u>**

The Institute shall have the following powers and duties to:

1/ Conduct study and research on existing policies and strategies to enrich and update them, initiate policy and strategy proposals considering the on-going progress and objective reality of the county;

2/ undertake studies and research, formulating new policy and strategy ideas and prepare policy and strategies documents;

3/ Conduct impact analysis, study and research on problems encountered during implementation of different policies and strategies and initiate remedial ideas;

4/ collect data it requires in the course of conducting its studies and research, establish a data base and to use those compiled by other bodies;

5/ organize forums, seminars and workshops to enhance policy study and research works; prepare and deliver short-term trainings in collaboration with appropriate bodies, as necessary publish and disseminate research outputs;

6/ render consultancy services in policy and strategy issues;

7/ establish relations with domestic and foreign institutions that may contribute towards the achievements of its objectives;

8/ Search out, organize and capacitate researchers having commitment, preparedness, knowledge and interest to implement the country's policies and strategies;

፱/ የዲሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግስት ተልዕኮን የሚያሳኩ የጥናትና ምርምር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ተቋማት ዓይነትና ተልዕኮ እንዲሁም ትስስር ምን መሆን እንዳለበት የውጭ ሀገር ልምድ የመቀመር፤

፲/ የሥርዓቱን ፖለቲካል ኢኮኖሚ በተቀመጠው ልማታዊ አቅጣጫ መገንባት የሚያስችሉ የመንግስት ድጋፍና አመራር የሚያጠናክሩና የኢኮኖሚውን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት የሚያረጋግጡ ተቋማት ግንባታ በተመለከተ ጥናትና ምርምር የማካሄድ እና መነሻ ሀሳብ የማቅረብ፤

፲፩/ የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በራሱ ስም የመክሰስና፣ የመከሰስ፤

፲፪/ ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን፡፡

## ፭. የኢንስቲትዩቱ አቋም

ኢንስቲትዩቱ፡-

፩/ በመንግስት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተር፣ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና

፪/ አስፈላጊው ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

## ፮. የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ስራ አስፈጻሚ ሆኖ የኢንስቲትዩቱን ስራዎች ይመራል፣ያስተዳድራል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኢንስቲትዩቱን ተመራማሪዎች፣ የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሰረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግስት በሚፀድቅ መመሪያ እና ሌሎች ሰራተኞች የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ እቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

9/ Compile foreign best practices and initiate proposals on the types, missions and interfaces of study and research and technology transfer institutions that enable to achieve the objective of a democratic developmental state;

10/ Conduct study and research and initiate proposals on building institutions that may strengthen government support and leadership to sustain the developmental direction of the country's political economy and to ensure the economy's competitiveness on the international sphere;

11/ Own property, enter into contract, sue and be sued in its own name;

12/ Carry out other related activities necessary for the attainment of its objectives.

## 5. Organization of the Institute

The Institute shall have:

1. A Director General and Deputy Director Generals to be appointed by the government and
2. The necessary staff.

## 6. Powers and Duties of the Director General

1. The Director General shall be the chief executive officer of the Institute and shall direct and administer the activities of the Institute.
2. Without limiting the generality of the provisions of Sub- Article 1 of this article, the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the Institute specified under Article 4 of this Regulation;

b) employ and administer researchers of the Institute based on directives approved by the Government following the basic principles of the federal civil service laws and other employees by the federal civil service laws;

c) prepare the work program and budget of the Institute and implement same upon approval;

d) effect expenditure in accordance with the work program and budget approved for the Institute;

ሠ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለፕላንና ልማት ኮሚሽን ያቀርባል፡፡

፫. ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ፯. <u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር</u>

፩/ የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል፤

፪/ በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፡፡

## ፰. <u>በጀት</u>

የኢንስቲትዩቱ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፡-

ሀ) በመንግስት ከሚመደብለት በጀት፤

ለ) አላማውን ለማሳካት ከሚያገኛቸው ማናቸውም ስጦታ፣ እርዳታ እና ሌሎች ገቢዎች ፤

ሐ) ከምክር አገልግሎት ክፍያዎችና ከሕትመቶች ሽያጭ ገቢ ይሆናል፡፡

## ፱. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየአመቱ ይመረመራሉ፡፡

## ፲. <u>ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>

የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል ለማቋቋም የወጣው ደንብ ቁጥር ፫፻፲፩/፪ሺ፯ እና የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲቲዩት ለማቋቋም የወጣው ደንብ ቁጥር ፶፬/፲፱፻፺፩ በዚህ ደንብ ተሽረዋል፡፡

e) represent the Institute in all its dealings with third parties;

f) prepare and submit to Planning And Development Commission, the performance and financial reports of the institute.

3/ The Director General may, to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Institute, delegate part of his powers and duties to other directors and employees of the Institute.

## 7. <u>Powers and Duties of the Deputy Director General</u>

1/ The Deputy Director General shall assist the Director General in planning, organizing, directing and coordinating the activities of the Institute;

2/ Perform other activities assigned by the Director General;

3/ Shall represent the Director General in his absence.

## 8. <u>Budget</u>

The Budget of the Institute shall be drawn from the following sources;

a) Budget allocated by the government;

b) Any donations and assistance made for the attainment of its objectives and any other incomes;

c) Consultancy service fees and proceeds from the sale of publications.

## 9. <u>Books of Accounts</u>

1/ The Institute shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Institute shall be audited annually by the Auditor General or by other Auditors assigned by him.

## 10. <u>Inapplicable laws</u>

The Policy Studies and Research Center Regulation No.311/2014 and The Ethiopian Development Research Institute Regulation No.54/1999 are here by repealed.

**፲፩. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር ፲ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ጠቅላይ ሚኒስትር**

**11. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of approval by the Council of Ministers.

**Done at Addis Ababa, this 19th Day of November, 2018.**

**ABIY AHMED (DR.)**
**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**